የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

# በኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን

## የጅማ ከተማ ፅዳትና ውበት ተሞክሮ



2017 ዓ.ም አዲስ አበባ

# ማውጫ

መግቢያ ..... 1
1. ክፍል አንድ፡-አጠቃላይ ሁኔታ ..... 2
1.1. ዓላማ ..... 2
1.1.1. ዋና ዓላማ ..... 2
1.1.2. ዝርዝር ዓላማዎች ..... 2
1.2. አስፈላጊነት ..... 2
1.3. ወሰን ..... 2
1.4. የመረጃ አሰባሰብ ስልት ..... 2
2. ክፍል ሁለት፡- ..... 3
2.1. ጅማ ከተማ ..... 3
2.1.1. የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ..... 3
2.1.2. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት ከተማው የነበረበት ሁኔታ ..... 3
2.1.3. የተከናወነ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ..... 4
2.1.4. የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች ..... 4
2.1.5. በተሰጠ ግንዛቤ የተገኘ ውጤት ..... 5
2.2. የተሟሉ ተሽከርካሪዎችና ቴክኖሎጂዎች ..... 6
2.3. የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ..... 6
2.4. በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት ..... 8
2.4.1. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ ..... 8
2.4.2. ደረቅ ቆሻሻን በአይነት የመለየት ስራ ..... 9
2.5. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ..... 9
2.6. የቀልዝ (ኮምፖስት) ዝግጅት ..... 11
2.7. (Effective Micro organizm (E.M)) ዝግጅት ..... 12
2.8. ቴክኖሎጂን የመጠቀም ሁኔታ ..... 13
2.9. ሞዴል መንደር ..... 14
2.10. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ኃላፊነትን ስለመወጣት ..... 14
2.11. በተሰሩት ልማት ሥራዎች የተፈጠረ የስራ ዕድል ..... 15

2.12. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ..... 15
2.13. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ምክንያት የተገኘ ማበረታቻ ..... 15
2.14. የከተማ ፅዳትና ውበት እንዲሁም የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች ..... 16
2.14.1. የኮሪደር ልማት ሥራ ..... 17
2.14.2. የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ ..... 20
2.15. በከተማው ከተከናወኑ የተቀናጀ የደረቅ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ እንዲሁም የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራ ውስጥ በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ ተግባራት ..... 23
2.15.1. በጋራ ተደጋግፎ መስራት ..... 23
2.15.2. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ ..... 23
2.15.3. ሞዴል መንደር መረጣ ..... 23
2.15.4. ቀልዝ (ኮምፖስት) ዝግጅት ..... 23
2.15.5. ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘ ሀብት መሆኑ ..... 24
2.15.6. የኮሪደር ልማት ስራ ..... 24
2.15.7. የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ ..... 24
3. ክፍል ሦስት፡- ..... 25
3.1. ማጠቃለያ ..... 25

# መግቢያ

ሀገራችን ዘላቂ ልማትን እውን ለማድረግ የልማትና የኢኮኖሚ ዕድገት ዘርፎችን ለማሳደግ እና የአካባቢ ጥበቃና አጠቃቀምን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አሳታፊና ያልተማከሉ የአካባቢ መንከባከቢያ ሥርዓቶችን በማዘጋጀት ተግባራዊ እያደረገች ትገኛለች፡፡ ይህም በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ የልማት መስኮች ዕድገት ለማስመዝገብ እየተደረገ ካለው በተጨማሪ ልማቱ ቀጣይ እንዲሆንና ለመጪው ትውልድ ከአካባቢና ተፈጥሮ ሀብቶችን በአግባቡ ተጠቅሞ በዘላቂነት ለማስተላለፍ እንዲቻል የተለያዩ የልማትና ዕድገት ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎችን፣ ፕሮግራሞችንና ዕቅዶችን እየተገበረች ትገኛለች፡፡ ለአብነትም የከተሞች ውበትና የወንዞች ዳር ልማቶች እና የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ በዋናነት የሚጠቀሱ ዘላቂ የአካባቢ አያያዝ ስርዓት ተግባራት ናቸው፡

ዜጎች ንጹህ እና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 44 ያስገነዝባል፡፡ስለሆነም በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ህብረተሰብን በማሳተፍ የሚከናወኑ በርካታ የአካባቢ ጥበቃ ስራዎች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ተግባራትም ጤናማ ማህበረሰብ ለመፍጠር ሚናቸው የጎላ ነው፡፡

የከተማ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ጉድለት የአብዛኞቹ የሀገራችን ከተሞች ችግር እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ለዚህም መነሻ ምክንያቶች ከሆኑት መካካል የህዝብ ቁጥር መጨመር፤ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ የህዝብ ፍልሰት እና በቆሻሻ አወጋገድ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም ዙሪያ በነዋሪዎች ዘንድ የሚታየው የግንዛቤ ጉድለት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው ፡፡በመሆኑም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ስርዓት ባለመዘርጋቱ እና በየከተሞቹ ጥንቃቄ በጎደለው ሁኔታ በየቦታው የሚጣለው ቆሻሻ ነዋሪዎችን ለተለያዩ በሽታዎች እያጋለጠ ስለሆነ ለጤናማ ህይወት አስቸጋሪ በመሆኑ ዋነኛ የማበረሰብ የቅሬታ ምንጭ እየሆነ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን በከተሞች የሚከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ተሞክሮዎችን በማሰባሰብ ለማፋትና ቀጣይ ለሚደረጉ የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራዎች በግብዓትነት ለመጠቀም የሚያስችሉ ሥራዎችን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡

ይህ የተሞክሮ ቅመራ ሰነድ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የጅማ ከተማን መሰረት ያደረገ ነው፡፡በጅማ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በማሻሻል ቆሻሻውን ከቤት ለቤት ልየታ ጀምሮ እስከ ቆሻሻ ማስወገጃያ ያለው ሂደት፤የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ የልማት ሥራዎች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እተሰሩ በመሆናቸው ለሌሎች መማሪያ ሆነው የሚታዩ ናቸው፡፡በመሆኑም በከተማው ውስጥ የተከናወኑ ለመልካም ተሞክሮ የሚሆኑ መረጃዎችን በማሰባሰብና በማጠናቀር ይህ ሰነድ ተዘጋጅቷል፡፡

# 1. ክፍል አንድ፡-አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1. ዓላማ

### 1.1.1. ዋና ዓላማ

በጅማ ከተማ አስተዳደር የተከናወኑ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎችን በመልካም ተሞክሮነት ቀምሮ በተለያዩ ስልቶች ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ፡፡

### 1.1.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- የጅማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን በመልካም ተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች ከተሞች ከዚህ ተምረው የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ማድረግ
- የጅማ ከተማን የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎችን መነሻ በማድረግ ሌሎች ከተሞች እንደየአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ከተማቸውን ጽዱና ውብ እንዲያደርጉ ማስቻል፡፡

## 1.2. አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 44 ዜጎች ጽዱና ጤናማ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው በሚል በተቀመጠው መሰረት ከተሞችን ጽዱና አረንጓዴ በማድረግ ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚደረገው እንቅስቃሴ ጠቃሚ ነው፡፡ በመሆኑም በጅማ ከተማ የተከናወኑ መልካም ስራዎችን በተሞክሮነት ቀምሮ ሌሎች እንዲማሩበትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 1.3. ወሰን


የተሞክሮ ቅመራው የተከናወነው በኦሮሚያ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በጅማ ከተማ አስተዳደር የተተገበሩ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ እንዲሁም የኮሪደር እና ወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ላይ ያተኮረ ነው፡፡

## 1.4. የመረጃ አሰባሰብ ስልት

በሥራው ሂደት ተሞክሮን ለማሰባሰብ የሚረዳ ቼክ ሊስት በማዘጋጀት አስቀድሞ ለክልልና ለከተማ አስተዳደሩ በመላክ ይዘቱን ቀድመው እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡ በመቀጠልም የባለሙያዎች ቡድን በሥራው ላይ እንደተሠማራ በቅድሚያ ከክልሉ የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን እና ከከተማ አስተዳደሩ አካባቢ ጥበቃ እንዲሁም ማዘጋጃ ኃላፊዎችና ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች ጋር ስለ አላማው ዝርዝር ሁኔታ በመወያየት በተለያየ ስልት መረጃ ተሰባስቧል፡፡

መረጃ አሰባሰቡም የተዘጋጀውን ቼክ ሊስት በመጠቀም ሲሆን ለዚሁ ተግባር የሚጠቅሙ ሰነዶችን በመፈተሸ፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ስራ ላይ የተደራጁ የማህበር አባላትን፣ ሌሎች ተጠቃሚዎችንና ባለሙያዎችን በማነጋገር እና ሥራው በሚከናወንበት ቦታ ተገኝቶ የመስክ ምልከታ በማድረግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡

በማጠቃለያም ከጅማ ከተማ አስተዳደር ማዘጋጃና አካባቢ ጥበቃ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመረጃ አሰባሰቡ እና በመስክ ምልከታው በታዩና በተነሱ ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት ተደርጎ ተጨማሪ መረጃ ተወስዷል።




ፎቶ ፡- መረጃ በተለያየ ስልት ሲሰበሰብ

# 2. ክፍል ሁለት፡-

## 2.1. ጅማ ከተማ

ጂማ ከተማ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ከአዲስ አበባ 352 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ከተማዋን በሰሜን መና ወረዳ፤በደቡብ ሰቃ ወረዳ፤በምስራቅ ቀርሳ ወረዳ እና በምዕራብ ዴደ ወረዳ ያዋስኗታል።ጅማ ከተማ በፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ ከተሞች አንዷ ስትሆን የከተማዋ የህዝብ ብዛት 195,228 ከዚህ ውስጥ 40,450 አባወራ እና እማወራ መሆኑን የቅርብ ጥናቶች ያሳሉ። በሌላ በኩል በ17 የከተማ ቀበሌዎች የተከፈለች ከተማ ነች ።

### 2.1.1. የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ

### 2.1.2. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስራ ከመጀመሩ በፊት ከተማው የነበረበት ሁኔታ

በፊት የጅማ ከተማ ደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስርአት በርካታ ችግሮች የነበሩበት ሲሆን ለዚህም መነሻ ከሆኑት ምክንያቶች መካከል በከተማው የህዝብ ቁጥር መብዛት፣በከተማው የአረንጓዴ ልማት አለመኖር፣ቆሻሻን ለማፅዳት ቢሞከርም ያልተደራጀ አሰራር መሆኑ እና ከተማውን የሚመጥን እድገትን መሰረት ያደረገ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ያለመዘርጋት የመሳሰሉ ናቸው።በከተማው ቀደም ሲል የነበረው የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት ኃላፊነት በጎደለ ሁኔታ የትም ቦታ የሚጠራቀም ነበር።ከቤት ለቤት፣ከተለያዩ ሆቴሎችና ሌሎች የንግድና ማምረቻ ተቋማት፣ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች እንዲሁም ከመንግስት ተቋማት ይወጣ የነበረው ደረቅ ቆሻሻ የከተማውን ገጽታ

ከማበላሸቱም በላይ የአየር ብክለት በመፍጠር ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሆኖ ነዋሪዎችን በእጅጉ ይጎዳ እንደነበርና እንስሳቶች የወዳደቁ ፌስታሎችን በመመገብ ለሞት እየተጋለጡ ነበር፡፡

በዚያን ወቅት የነበረ የደረቅና ፍሳሽ ቆሻሻ ጥርቅም የወባ ትንኞች እንዲራቡ ምክንያት ሆኖ ነዋሪዎች ለወባ በሽታ የተጋለጡበት ወቅትም ነበር፡፡ በተጨማሪም ቆሻሻ ማስወገጃና ማጠራቀሚያ ቦታዎች በበቂ ሁኔታና በጥንቃቄ ያልተደራጁ በመሆኑ የሚመነጨዉ ቆሻሻዎች በየመንገዱና በየመኖሪያ መንደሮች ሥርዓት በሌለው ሁኔታ በየቦታው ይጣሉ ነበር፡፡ በተጨማሪም በየመንገዱ የሚገኙ ቦዮች በሚጣል ቆሻሻ ስለሚደፈኑ በዝናብ ወቅት መንገዶች በጎርፍ እየተጥለቀለቁ ለመተላለፍ ያስቸግሩ ነበር፡፡ በሕብረተሰቡ ዘንድ ቆሻሻን ለማጽዳት ኃላፊነቱን የሚወስደው አንድ ድርጅት ብቻ ማለትም ማዘጋጃ ቤት ነው ተብሎ ይታመን ስለነበር አካባቢን በማጽዳት ‹አይመለከተኝም› የሚል አሳቤ ነበራቸው፡፡ ከግንዛቤ እጥረት የተነሳም ቆሻሻ ጉዳት ብቻ እንጂ ምንም ጥቅም እንደሌለው አድርገው ያስቡ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በከተማው የዘመነ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ባለመዘርጋቱ ምክንያት ከፍተኛ የሆነ የመልካም አስተዳደር ችግር ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ በመሆኑም በከተማ ይህንን ችግር ለመፍታት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡ ስለሆነም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ሥርዓት በመዘርጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ ተጨባጭ ለውጥ እንዲታይ ሆኗል፡፡

### 2.1.3. የተከናወነ የቅድመ ዝግጅት ሥራ

በቆሻሻ ምክንያት በከተማው ውስጥ እየተፈጠረ ያለውን ማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና አካባቢያዊ ችግር በመለየትና በማጥናት ወደ መፍትሔ ማፈላለግ ተግባር ተገብቷል፡፡ወደ ተግባር ሲገባም በመጀመሪያ “የጅማ ከተማን ጽዱ፣ውብና አረንጓዴ ከተማ ማድረግ” በሚል መሪ ሀሳብ ዕቅድ ታቅዶ ለአመራሩ፣ለባለሙያዎች፣ለባለሀብቶች፣ሀገር ሽማግሌዎች፣ለታዋቂ ግለሰቦች እና ለማሕበረሰቡ በዕቅዱ ላይ ግንዛቤ በመፍጠር ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ መተማመን ላይ ተደረሰ፡፡አባላትን በመለየትና ማሕበራትን በማደራጀት ወደ ስራ ማስገባት እንዲሁም በየቀበሌው አደረጃጀት በመፍጠር የከተማው የጽዳት አሰራር ስርአት እንዲይዝ የመምራት፣የመደገፍ እና የማስተባበር ስራ በመስራት ሁሉም ትኩረት እንዲሰጠው ተደረገ፡፡ የጽዳት ዘመቻ የጊዜ ሰሌዳ በማቀድ ክንውኑን በመከታተልና በመገምገም ስራዎች በትኩረት እንዲሰሩ አቅጣጫ ተቀምጦ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 2.1.4. የተከናወኑ የግንዛቤ ሥራዎች

ቀደም ሲል ከተለመደው ስርአት የሌለው የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ተላቆ ትክክለኛ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ ስርአት ለመፍጠር በተለያየ ጊዜ ለተለያዩ አካላት የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረኮች ተዘጋጅተዋል፡፡ግንዛቤው የተፈጠረው ለከተማ እና ለቀበሌ አመራሮች፣ለተደራጁ ማህበር አባላት፣ለሚመለከታቸው ባለሙያዎች፣ለባለሀብቶች፣ለማሕበረሰቡ ሲሆን በአጠቃላይ ከ20ıı ዓ.ም ጀምሮ በተከታታይ ዓመታት ለበርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች ሰፊ ግንዛቤ ተፈጥሯል፡፡ለነዚህ አካላት ግንዛቤ የተፈጠረበት ርዕስ ስለ የከተማ ቆሻሻ አሰባሰብ፣አያያዝና አወጋገድ፣ስለ አካባቢ ተፅኖ ግምገማ፣ከተማን ማስዋብ ሲሆን በአጠቃላይ ዋና እቅዱን መሰረት ያደረገ ነው፡፡የግንዛቤ አሰጣጡ አንድ ባለሙያ ሁለት(2) ቀበሌዎች በኃላፊነት ይዞ በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት በሳምንት ሦስት ቀናት(ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ) በያዘው ቀበሌ ግንዛቤ ሲፈጠር ቆይቷል፡፡በተጨማሪም በት/ቤት ደረጃም የአካባቢ እንክብካቤ ክበብ እንዲጠናከር ድጋፍ እየተደረገ ይገኛል፡፡በሌላ በኩል ብሮሸርና በራሪ ወረቀት በማዘጋጀት ለሕብረተሰቡ ተደራሽ ማድረግ የተቻለ ከመሆኑም በላይ በፋና እና OBN ሬዲዮ የአየር ሠዓት ተገዝቶ የግንዛቤ መልዕክት እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡




ፎቶ 2፡- የግንዛቤ ፈጠራ መድረኮች

### 2.1.5. በተሰጠ ግንዛቤ የተገኘ ውጤት

አንድን ነገር ለማከናወን መጀመሪያ የግንዛቤ መፍጠር ስራን ማስቀደም ውጤታማ ያደርጋል፡፡በመሆኑም የጅማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድን ስርአት ለማስያዝ እንዲሁም ከተማዋን ጽዱና ውብ ለማድረግ የግንዛቤ መፍጠር ስራዎችን አከናውኖ በሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ላይ የተሻለ ለውጥ ማምጣት ተችሏል፡፡በመሆኑም ህብረተሰቡ በፊት የነበረውን አስተሳሰብ አሻሽሎ አሁን ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንዳለበት ተገንዝቧል፡፡ሌሎች ቆሻሻ ያለአግባብ ሲጥሉ ሲያይ ጥቆማ መስጠት እንዲሁም ‹የበከለ ይከፈል› የሚለውን መርህ በመከተል አስፈላጊውን ለመፈፀም ሙተማመን ላይ የተደረሰ መሆኑና ደረቅ ቆሻሻ ሀብት መሆኑን ሰው ሁሉ አውቆ ያገኘውን ግንዛቤ ወደ ተግባር በመቀየር የመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀም ችሏል፡፡ በተለይ በሞዴል መንደር ያሉ ነዋሪዎች ያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ በየአይነቱ በመለየት ለሚሰበስቡ ማህበራት በአግባቡ ማስረከብ ችለዋል፡፡በአጠቃላይ የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ አያያዙና አወጋገዱ ስርአት ስለያዘ ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ባለመያዙ ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ቀንሰዋል፡፡ የከተማውም ፅዳትና ውበት እንዲሻሻል የተፈጠረው ግንዛቤ ያመጣው ውጤት ነው፡፡

## 2.2. የተሟሉ ተሽከርካሪዎችና ቴክኖሎጂዎች

በጅማ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለመተግበር የሚያገለግሉ በርካታ ግብአቶች እንዲሟሉ ጥረት ተደርጓል፡፡ ለአብነትም በእጅ የሚገፉ ጋሪዎች ባለ1ሜ.ኩብ 80፣ በከተማው ዳርቻ ላይ ላሉ መንደሮች የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች 10፣ገንዳውን የሚያነሱ ስኪፕ ሎደሮች 3፣ ለቆሻሻ ማጓጓዣ ተሳቢ ያለው ትራክተሮች 6፣ ሲኖትራኮች 5፣ ለመጫኛ የሚያገለግል ሎደሮች 2፣ ግሬደር 1፣ በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ላይ ለማስተካከል የሚያገለግል ዶዘር 1 እና የሚጠቀጥቅ ሮሎ 1 የመሳሰሉ ያሉ ሲሆን ባለቤትነታቸውም የከተማው ማዘጋጃ ቤት ነው፡፡ እነዚህ ግብአቶች(ማቴሪያሎች) በዋናነት የሚያገለግሉት ለደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ እና በከተማው ውስጥ ለሚከናወኑ መሰረተ ልማቶች ነው፡፡




ፎቶ 3፡- ለደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት መከናወኛ ካሉት ማቴሪይሎች ውስጥ ውስኖቹ

## 2.3. የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

በከተማው የሚታዩ ችግሮችን በማጤን እና ለችግሮቹ መፍትሔ ለመስጠት በዕቅድ የተመሩ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በመቀጠልም የተከናወነው ተግባር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ ሲሆን ግንዛቤውም ውጤት አስመዝግቧል፡፡ የሕብረተሰቡ አስተሳሰብ ተሻሽሎ በተነሳሽነት የድርሻቸውን ተግባራት በማከናወናቸው ዛሬ ከድሮው በተሻለ ንጽህና ላይ የምትገኘውን ጅማ ከተማ ማየት ተችሏል፡፡

ከቆሻሻ አመንጪዎች ጋር በመግባባት የጽዳት ዘመቻ ስራ በማሰራት፣በጽዳት ላይ ለሚሰሩ ማህበራት ክፍያ እንዲከፍሉ በማድረግ፣ደረቅ ቆሻሻን በየአይነቱ እየለዩ በአግባቡ ለሚሰበስቡ ማህበራት እንዲያስረክቡ በማድረግና ድጋፍ በሚያስፈልግ ቦታ ላይ ድጋፍ በስጠት የተዘጋጁ ግብአቶችን(ማቴሪያሎችን) በአግባቡ በመጠቀም የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስርአቱ በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡

በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስራ የሚሰሩ ማሕበራት በማቋቋምና ውል በመዋዋል እንዲሁም ተግባርና ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማድረግ ስራው በተሳካ መልኩ እንዲከናወን ተደርጓል፡፡የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በማዘጋጀት የሚወገድ ቆሻሻ በአግባቡ እንዲወገድ በማድረግ ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ደግሞ ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል ተችሏል፡፡

የከተማ ፅዳትና ውበት፣የኮሪደር ልማት እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎችን በመስራት ከተማዋን ጽዱና ውብ እንድትሆን ተደርጓል፡፡በአሰራሮች ላይ ጥብቅ ክትትል፣ቁጥጥርና ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም የተሰሩ ስራዎችን በመገምገም በተሻለ ሁኔታ ስራው ቀጣይነት እንዲኖረው ተደርጓል፡፡ ከአመራሮችና ባለሙያዎች በተጨማሪ ታዋቂ ባለሀብቶችና የአካባቢ ሽማግሌዎች በስራው ክትትልና ድጋፍ ላይ ተሰማርተዋል፡፡

በ2013 ዓ.ም ባለሀብቶች አልባሳት እንዲሁም በእጅ የሚገፋ ጋሪ ገዝተው ለማህበራት በመስጠት ለስራው መጠናከር አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡በስራው ላይ ትኩረት ሰጥተው የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡ ግለሰቦችን በመምረጥ የጽዳት አምባሳደርነት ማዕረግ በመስጠት የማበረታታት ስራ ተሰርቷል፡፡ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለጅማ ከተማ አስተዳደር ለማበረታቻ የእውቅና ምስክር ወረቀት ተሰጥቷል፡፡







ፎቶ 4፡-ማህበረሰቡ በጽዳት ዘመቻ ላይ

## 2.4. በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ፣ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ ማሕበራት

በጅማ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ላይ ለመስራት የተደራጁ 40 ማህበራት ያሉ ሲሆን ሁሉም ከቤት ለቤት፣ከመንግስትና ከግል ተቋማት ደረቅ ቆሻሻ የማሰባሰብ ስራ የሚሰሩ ማህበራት ናቸው፡፡ እነዚህ ማህበራት በተለያዩ ቀበሌዎች የሚገኙ ሆነው ተጠሪነታቸው ለየቀበሌው ጽዳትና ውበት ቡድን ነው፡፡ ስለዚህ የቀበሌው ጽዳትና ውበት ቡድን በዋናነት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በተጨማሪም የከተማው ማዘጋጃ ቤትም ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ማህበራቱ ሁሉም የየራሳቸው አባላት ያሏቸው ሲሆን በአጠቃላይ ወ 147 ሴ 343 ድ 490 አባላት ይገኛሉ፡፡ ማህበራቱ ከማዘጋጃ ቤት ጋር ውል ተዋውለው ተግባርና ኃላፊነታቸውን በውሉ መሰረት እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ በሌላ በኩል በኮንትራት ተቀጥረው በዚሁ የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች አሉ፡፡ እነሱም በመንገድ ጥርጊያ ላይ የተሰማሩ 356፣ የቦይ ጽዳትን የሚሰሩ 27፣ በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ግቢ ውስጥ ደረቅ ቆሻሻን በአይነት የመለየት ስራ የሚሰሩ እና ቀልዝ (ኮምፖስት) የሚያዘጋጁ 58 በአጠቃላይ 441 ሰራተኞች ስራውን በማከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡




ፎቶ 5፡- የማህበራትመግባቢያና ውል ሰነድ

### 2.4.1. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ

በየግለሰቡ ቤት ያለ ደረቅ ቆሻሻ መጀመሪያ ሁሉም ነዋሪ በየቤቱ ደረቅ ቆሻሻውን በየአይነቱ በመለየት በቆሻሻ ማጠራቀሚያ በ3 አይነት ከረጢት (በማዳበሪያ) በግቢያቸው ያጠራቅማሉ፡፡ አለያየቱም ቆሻሻውን ያመነጩት ሰዎች የሚበሰብስ ቆሻሻን በአረንጓዴ ከረጢት ፣ የፕላስቲክ ቆሻሻን በቢጫ ከረጢት እና የጠርሙስና መስታወት ስብርባሪን ደግሞ በቀይ ከረጢት በመለየት ያስቀምጣሉ፡፡ በመቀጠል ቤት ለቤት የሚሰበስቡ ማህበራት በሳምንት ሁለት ጊዜ በተመደቡበት ሳይት/ ቦታ በመንቀሳቀስ የተጠራቀመውን ደረቅ ቆሻሻ በማንሳት ወደ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ያደርሳሉ፡፡የመንገድ ላይ ጥርጊያ በቀን

ሁለት ጊዜ ጠዋት እና ከሰዓት የሚከናወን ሲሆን የሚያጸዱ/የሚጠርጉ ሰራተኞች ደረቅ ቆሻሻውን ከሰበሰቡ በኋላ በየቦታው የተሰበሰበው ደረቅ ቆሻሻ በዛኑ እለት የኮንትራት ሰራተኞችን በመጠቀም በማዘጋጃ ይነሳና ወደ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ይደርሳል፡፡በተጨማሪም በመንግስትና በግል ተቋማት የሚመነጭ ደረቅ ቆሻሻ የሚነሳው በማዘጋጃ አማካኝነት ሆኖ የማንሻ ጊዜው እንደ ቆሻሻው ብዛት ሁኔታ ታይቶ ሲሆን የሆቴሎች በየቀኑ ይነሳል፡፡

### 2.4.2. ደረቅ ቆሻሻን በአይነት የመለየት ስራ

የደረቅ ቆሻሻ የመለየት ስራው የሚከናወነው ከቤት ለቤት ጀምሮ ነው፡፡ አለያየቱም የሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ በአረንጓዴ ከረጢት(ማዳበሪያ)፣ የፕላስቲክ ቆሻሻ በቢጫ ከረጢት(ማዳበሪያ) እና ብረታብረት፣የጠርሙስ ስባሪና የመስታወት ስብርባሪ በቀይ ከረጢት(ማዳበሪያ) ተለይቶ ይቀመጣል፡፡ በተጨማሪ ቆሻሻው በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ከደረሰ በኋላ በአግባቡ ለማጣራት ሲባል በተጨማሪ ልየታው በጥንቃቄ ይከናወን እና ተፈላጊ የሆነው ወደሚፈለገው ቦታ ሲላክ የማይፈለገው ደግሞ ወደ ማስወገጃ ቦታ ተወስዶ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡ ፕላስቲክ፣ብረታብረት፣ጎማ፣የጠርሙስና መስታወት ስብርባሪዎች ተረካቢ እስኪገኝ በደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ግቢ ውስጥ በተመረጠ ቦታ ተለይቶ ለብቻ ተከማችቷል፡፡



ፎቶ 6፡- ደረቅ ቆሻሻ ቤት ለቤት ሲለይ ማጠራቀሚያ ከረጢት(ማዳበሪያ)

## 2.5. የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill)

በጅማ ከተማ ፣ የደረቅ ቆሻሻ ጊዚአዊ መቀባባያ ቦታ ያለ ሲሆን የሚገኘው መርካቶ መሀል ነው፡፡በዚህ ቦታ የሚመጣ ደረቅ ቆሻሻ ይሰበሰብና ወደ ማስወገጃ ቦታ ይወሰዳል፡፡

በጅማ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ይገኛል፡፡ ማስወገጃ ቦታው የሚገኘው ከከተማው 10 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ሲሆን ስፋቱ 10 ሄክታር ነው፡፡በአሁኑ ሰዓት 3.5 ሄክታሩን እየተገለገሉበት ይገኛል፡፡ይህ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ(sanitary land fill) በ2010 ዓ.ም በULDP ድጋፍ የተሰራ ነው፡፡ቦታው የተዘጋጀው በጥናት ከከተማው የራቀ ስለሆነ በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡አሰራሩ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ከስር በጆሜምብሬን የተነጠፈ በመሆኑ ፈሳሽ ነገር ሲፈጠር ወደ መሬት አይሰርግም፡፡ለፈሳሹ ነገር ማሳለፊያ ቱቦ ያለ ሲሆን ፈሳሹን የሚቀበሉ 6 ጉድጓዶች አሉ፡፡ በጉድጓዶቹ ውስጥም የሚያልፍ ፈሳሽ ውሃ በተዘጋጀው ቴክኖሎጂ ተጣርቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ቦታው የሚተዳደረውም በማዘጋጃ ባለቤትነት ነው፡፡በዚህ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ግቢ ውስጥ 60 ሰራተኞች የሚሰሩ ሲሆን ሁለቱ (ማናጀሩ እና ጥበቃው) ቋሚ ሰራተኛ ሆነው ቀሪዎቹ በኮንትራት ተቀጥረው በመስራት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ሰራተኞቹ ደረቅ ቆሻሻን በመለየት ፣በቀልዝ(ኮምፖስት) ዝግጅት እና በግቢ ውስጥ ያሉ ችግኞችን በመንከባከብ ስራ ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡




ፎቶ 7፡-የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill)

## 2.6. የቀልዝ (ኮምፖስት) ዝግጅት

የቀልዝ (ኮምፖስት) ዝግጅት ስራው የሚከናወነው በዚሁ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (sanitary land fill) ክልል ውስጥ በተዘጋጀው ሼድ ውስጥ ነው፡፡ የተዘጋጀው ኮምፖስትም በከተማ ውስጥ ለሚከናወኑ የአርንጋዴ ልማት ስራዎች የአፈርን ለምነት በማሻሻል በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ በ2016 በጀት ዓመት 50,000 ኪዩቢክ ሜትር ኮምፖስት ተዘጋጅቶ የተሰራጨ ሲሆን በ2017 ዓ.ም ሰፊ የሆነ ኮምፖስት እየተዘጋጀ ይገኛል ::







ፎቶ 8፡- ቀልዝ(ኮምፖስት) በመዘጋጀት ላይ ሳለ

## 2.7. (Effective Micro organizm (E.M)) ዝግጅት

በዚሁ ግቢ ውስጥ Effective Micro organizem (E.M) ይዘጋጃል::ይህም (E.M) በ2016 ዓ.ም 10,000 ሊትር ተዘጋጅቶ በኮምፖስት ዝግጅት ላይ የተጠቀሙት ሲሆን በተጨማሪም ለቄራ፣ለት/ቤት፣ለመንግስት ተቋማት እና ለጤና ጣቢያዎች በማከፋፈል መጥፎ ሽታ ያላቸው ነገሮች ላይ በመጨመር የተፈጠረው መጥፎ ሽታ እንዲጠፋ በማደረግ ግልጋሎት ላይ እየዋለ ይገኛል ::



ፎቶ 9:- የተዘጋጀ Effective Micro organizem (E.M)

የጠርሙስና የመስታወት ስብርባሪ እንዲሁም የፕላስቲክ ክምችት

የጠርሙስና የመስታወት ስብርባዎችን እንዲሁም ፕላስቲኮችን ከሌሎች ቆሻሻ ለብቻ በመለየት በየአይነታቸው ተከማችተው የተቀመጡ ሲሆን ተረካቢዎች ሲመጡ ለማስረከብ በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ::






ፎቶ 10፡- ጠርሙዝ፣ መሰታወትና፣ ፕላስቲኮች

## 2.8. ቴክኖሎጂን የመጠቀም ሁኔታ

በጅማ ከተማ የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአትን ለመጠቀም ሲባል የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ተችሏል፡፡ይህ ቴክኖሎጂን የመጠቀም ስርዓትም ቆሻሻው በአግባቡ እንዲወገድ እና ጥቅም መስጠት እንዲችል አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡እንዲሁም ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘና ከተጠቀሙበት ሀብት እንደሆነ በተግባር እንዲታይ አድርጓል፡፡በጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አስተባባሪነት ቀለሙ ቀይ፣ቢጫና አረንጓዴ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት (ማዳበሪያ) በመጠቀም ደረቅ ቆሻሻ በየአይነቱ ተለይቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለተጠቃሚ ማስረከብ ተችሏል፡፡ይህ ኮምፖስት ሲዘጋጅ እንዳይሸት የሚያደርግ እና የመበላላቱን ሂደት የሚረዳ ፈሳሽ(Effective Micro organizem (E.M)) በማዘጋጃት ይጠቀማሉ፡፡ ይህን ፈሳሽ(Effective Micro organizem (E.M)) መጥፎ ሽታ ያላቸው ነገሮች ላይም በመጨመር ሽታውን ለማጥፋት ጥቅም ይሰጣል፡፡የፕላስቲክ ጠርሙሶች እና የማዳበሪያ ከረጢቶችን ለችግኝ ማፍያ ፖት በመጠቀም መገልገል ተችሏል፡፡



ፎቶ 11፡- (Effective Micro organizem (E.M)) የሚዘጋጅበት ማቴሪያልና የተዘጋጀው

## 2.9. ሞዴል መንደር

በጅማ ከተማ በ2016 ዓ.ም 20 እና በ2017 ዓ.ም እስከ ታህሳስ ወር 13 ሞዴል መንደሮች ተፈጥረው በአሁኑ ወቅት (እስከ ታህሳስ 2017 ዓ.ም) 33 ሞዴል መንደሮች ይገኛሉ ::







ፎቶ 12፡- የተመረጡ ሞዴል መንደሮች በከፊል

## 2.10. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ኃላፊነትን ስለመወጣት

በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ሁሉም ኃላፊነቱን አውቆ ግዴታውን እንዲወጣ ተደርጓል::ይህ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ሲጀመር ማዘጋጃ ቤቱ ከማህበራት ጋር ውል የተዋዋለ ሲሆን ማህበረሰቡም ተግባር እና ሃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት ሰፊ የሆነ የግንዛቤ ፈጠራ ስራ በመስራት ነው:: በመሆኑም ሁሉም ማሕበራት እንደየ ስራ ድርሻቸው ግዴታቸውን ሲወጡ የህብረተሰቡ እና የተቋማት ግዴታ ከሆነው ውስጥ አንዱ ለስራው ማስፈጸሚያ ክፍያ መክፈል ነው:: ተጠቃሚዎች (ከፋዮች) እንዴትና ምን ያህል መክፈል እንዳለባቸው በካቢኔ እና በሚመለከታቸው ተወካዮች

ታይቶና ጸድቆ በስራ ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ነዋሪዎች የሚከፍሉት ከጣራና ግድግዳ ግብር ክፍያ ጋር ተጨምሮ በዓመት አንድ ጊዜ ሆኖ ሰፊ ካ.ሜ ያለው አባወራ ወይም እማወራ ፣000 ብር ሲከፍል ጠባብ ካ.ሜ ያለው አባወራ ወይም እማወራ ደግሞ 700 ብር ይከፍላል፡፡የመንግስት ተቋማት በዓመት እስከ ፣000 የሚከፍሉ ሲሆን የግል ተቋማት ደግሞ እንደ ስፋቱ የክፍያው መጠን ይለያያል፡፡ሆቴሎች፣ ቁርስ ቤቶች፣ሱቆች እና መሰሎቹ እንደ ቆሻሻ አመንጪነታቸው መጠን የተለያየ ሆኖ ትልቁ ፣800 ብር የሚከፍል ሲሆን ትንሹ 800 ብር በዓመት ይከፍላል፡፡ የልማት ተቋማት እንደ ቴሌ፣መብራት ኃይል፣እንሹራንስ እና ባንክ የሆኑት በዓመት እስከ 2,000 ብር ይከፍላሉ፡፡በተለያዩ ፕሮግራሞች ምክንያት ከተለመደው መጠን በላይ ቆሻሻ የሚያመነጭ ግለሰብ ወይም ተቋማት ቢያጋጥሙ ተጨማሪ ክፍያ አይጠየቁም፡፡ በማንኛውም አካል ክፍያው ሲፈፀም ለዚህ ለተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ማስፈፀሚያ ለተከፈለ ብር ሕጋዊ ደረሰኝ ለብቻው ተሰርቶ ይሰጣል፡፡

## 2.11. በተሰሩት ልማት ሥራዎች የተፈጠረ የስራ ዕድል

በዋናነት በተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ በማህበር ተደራጅተው እየሰሩ ያሉት ሰራተኞች ወ 17 ሴ 343 ድ 490 ሲሆኑ በኮንትራት ተቀጥረው እየሰሩ ያሉ ሰራተኞች ደግሞ 441 ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት አብዛኞቹ ተሳታፊዎች ሴቶች እንደሆኑ እና 80% ወጣቶች እንደሆኑ መረጃውን የሰጡን ባለሙያ ገልጸውልናል፡፡

## 2.12. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ያለው ቅንጅታዊ አሰራር

የከተማው ማዘጋጃ ቤት እና አካባቢ ጥበቃ መ/ቤት ዕቅዳቸውን በጋራ በማቀድ ስራውን በጋራ እየሰሩ ክትትልና ቁጥጥር እያደረጉ የስራውን ቀጣይነት እያጠናከሩ መሆኑን የከተማው ማዘጋጃ እና አካባቢ ጥበቃ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

## 2.13. በተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አሰራር ምክንያት የተገኘ ማበረታቻ

ከተማ አስተዳደሩ በቀበሌዎች ያሉ ስራዎችን በየ6 ወሩ በመገምገም ሞዴል መንደር ለፈጠሩ ቀበሌዎች እውቅና የሰጠ ሲሆን በነኛው በጀት ዓመት ነኛ ለወጣ ቀበሌ ነሞተር እንዲሁም በ2ኛው በጀት ዓመት ነኛ ለወጣ ቀበሌ ነሞተር በመስጠት የማበረታቻ ስራ ተሰርቷል፡፡ እንዲሁም የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለጅማ ከተማ አስተዳደር ለማበረታቻ የሚሆን የእውቅና ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡


የከተማና መሠረተ-ልማት ሚኒስቴር
MINISTRY OF URBAN AND INFRUSTRUCTURE
የዕውቅና የምስክር ወረቀት

ለ ጅማ ከተማ አስተዳደር

በ2016 በጀት ዓመት በተካሄደው በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ አገልግሎት አፈጻጸም ምዘና ግሩም ውጤት በማስመዘገብ በምድቡ አንደኛ ደረጃ ያገኘ በመሆኑ ይህ የእውቅና ምስክር ወረቀት ተሰጥቶታል።

ፎቶ 13፡- ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለጅማ ከተማ አስተዳደር ለማበረታቻ የተሰጠ የእውቅና ምስክር ወረቀት

## 2.14. የከተማ ፅዳትና ውበት እንዲሁም የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራዎች


የጅማ ከተማ "የጅማ ከተማን ጽዱ፣ውብና አረንጓዴ ከተማ ማድረግ" የሚል አላማ በመንደፍ ከተማዋን ውብ ለማድረግ ወደ ስራ ከገባች ሰነባብታለች። ከተማዋ በፊት ቆሻሻ መጣያ የነበሩና በስርአት ያልተያዙ ቦታዎች በማልማት አሁን ተለውጠው በመዝናኛነት አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ።ከተማዋ ቆሻሻን በማፅዳት፣መዝናኛ ቦታን በመፍጠር፣፣የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማትን በመስራት ውብ ገፅታ ያላት ከተማ ለመባል በጅምር ስራዋ ላይ ትገኛለች።




ፎቶ 14፡- በከተማው ካሉት መዝናኛ ቦታዎች አንዱ

### 2.14.1. የኮሪደር ልማት ሥራ

የኮሪደር ልማት ስራ በጅማ ከተማ የተጀመረው መስከረም በ2017 ዓ.ም ሲሆን የቅድመ ሁኔታ ስራዎች በፊት ተሰርተዋል፡፡ የኮሪደር ስራው በአሁኑ ወቅት (ከመስከረም እስከ ታህሳስ/2017 ዓ.ም) እየተሰራ ያለው ከኤርፖርት እስከ አዌቱ ግራንድ ሆቴል ያለው በሦስት ተከፍሎ ከአዌቱ ግራንድ እስከ ቴሌ 1.1 ኪ.ሜ ርዝመት ፣ከቴሌ እስከ ቤተ-መንግስት መግቢያ 1.4 ኪ.ሜ ርዝመት ፣ከቤተ-መንግስት እስከ ኤርፖርት 500 ሜ ርዝመት በሚል እየተሰራ በመጠናቀቅ ላይ ይገኛል፡፡ይህ ልማት እስከ 3 ኪ.ሜ ርዝመት እና እስከ 10 ሜ ስፋት ያለው የኮሪደር ልማት ነው፡፡ለመጠናቀቅም 95% ላይ እንደደረሰ መረጃውን የሰጡን የኮንስትራክሽን ባለሙያ ገልፀውልናል፡፡የኮሪደሩ ልማት ያካተታቸው በመንገዱ ግራና ቀኝ የአረንጓዴ ልማት ስራ፣ የእግር መንገድ፣የብስክሌት መንገድ፣ማየት ለተሳናቸው መንገድ፣በአረንጓዴ አሸብርቀው ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ የተሰሩ መዝናኛዎች፣ዘመናዊ መብራቶች፣የመኪና ማቆሚያዎች አሁን ባለበት ሁኔታ የሚታዩ ሲሆኑ የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ካሜራዎች፣ካፍቴሪያዎችና ሌሎችንም ለማሟላት መስመሮቹ የተዘረጉ ናቸው፡፡






አደባባይ አካባቢ







የስቴዲየም ጎን መዝናኛ







ፎቶ 15፡- የተሰሩ ኮሪደር ልማቶች በከፊል


### 2.14.2. የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ

የወንዝ ዳርቻ ልማትን በተመለከተ በአዌቱ ወንዝ 3 ቦታ ላይ እና በዶሎሎ ወንዝ ፣ ቦታ ላይ የተሰሩ ሆኖ በአጠቃላይ 4 ቦታ ላይ የወንዝ ዳርቻ ልማት ለምቷል፡፡ ይህ የወንዝ ዳርቻ ልማት በአጠቃላይ 34,063 ካ.ሜ ቦታን ሸፍኖ ለምቷል፡፡ ወንዝ ዳርቻ ልማቱ ከመጀመሩ በፊት ቦታው የቆሻሻ መጣያ ቦታ ከመሆኑ የተነሳ አካባቢውና ወንዙ በቆሻሻ የተበከለ ነበር፡፡ከአካባቢው መሸተት የተነሳ በወቅት በአካባቢው ለማለፍ በጣም አስቸጋሪ ነበር፡፡ አሁን ከለማ በኋላ ግን መዝናኛ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡ይህንን ልማት ለማልማት መነሻ የሆነው የሀገር አቀፍ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮግራም መሰረት ተደርጎ በ urbun infrastructure Institutional Development program(UIIDP) ድጋፍ እና በማዘጋጃ ቤት በጀት የተሰራ ልማት ነው፡፡


የአዌቱ ወንዝ ዳርቻ ልማት ከፊል ገጽታ

(የሸንኮሬ ወንዝ ዳርቻ በሚልም ይጠራል)






ፎቶ 16፡- የአዌቱ ወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

የዶሎሎ ወንዝ ዳርቻ ልማት ከፊል ገጽታ

መግቢያና መዝናኛ አካባቢ










ፎቶ 17፡- የዶሎሎ ወንዝ ዳርቻ ልማት በከፊል

## 2.15. በከተማው ከተከናወኑ የተቀናጀ የደረቅ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ እንዲሁም የኮሪደርና የወንዝ ዳርቻ ልማት ስራ ውስጥ በመልካም ተሞክሮነት የሚወሰዱ ተግባራት

### 2.15.1. በጋራ ተደጋግፎ መስራት

በጅማ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓትን ተግባራዊ ሲደረግ የከተማው አመራሮችን፣ባለሙያዎችን፣ባለሀብቶችን እና አጠቃላይ ማህበረሰቡን በማሳተፍ ሁሉም ኃላፊነቱንና ግዴታውን አውቆ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ በማድረግ ከከተማ እስከ ቀበሌ ድረስ በቅንጅታዊ አሰራር የተሰራ እና እየተሰራ ነው፡፡ ከከተማ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ሁለት ሁለት ቀበሌዎች በኃላፊነት ይዘው በተቀመጠው ፕሮግራም መሰረት በሳምንት ሦስት ቀናት(ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ) በያዙት ቀበሌዎች የግንዛቤ ፈጠራና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ ይህ አሰራር የስራውን ቀጣይነት ያጠናከረዋል፡፡ የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ለጅማ ከተማ አስተዳደር ለማበረታቻ የእውቅና ምስክር ወረቀት ሰጥቷል፡፡ የዚህም ምክንያቱ የጅማ ከተማ በቅንጅት ተጠናክሮ በመስራት የደረጃ ባለቤት መሆን ችለዋል፡፡

### 2.15.2. የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ ሁኔታ

በጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት አስተባባሪነት ቀለሙ ቀይ፣ቢጫ፣አረንጓዴ የሆኑ የደረቅ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ከረጢት (ማዳበሪያ) በመጠቀም ከቤት ለቤት ጀምሮ ቆሻሻ በየአይነቱ ተለይቶ ወደሚፈለገው በማድረስ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርገዋል፡፡

### 2.15.3. ሞዴል መንደር መረጣ

በጅማ ከተማ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት እንዲሁም አካባቢያቸውን በጽዳት በመያዝና በማልማት እንቅስቃሴያቸው ታይቶ 33 ሞዴል መንደሮች ተመርጠዋል፡፡ በእነዚህ ሞዴል መንደሮች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ራሳቸውን በማደራጀት ወደ ልማት በመግባት፣ አካባቢያቸውን በጋራ በፕሮግራም በየሳምንቱ በማፅዳት፣የሚነገራቸውን የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ተቀብለው በመጠቀም እና ለሌሎች መንደሮች አርአያ ሆነው ስለተገኙ ሞዴል መንደር ተብለው ሊመረጡ ችለዋል፡፡ ያገኙትን ግንዛቤ በመጠቀም ወደ ተግባር ለውጠው ቆሻሻ በአግባቡ እንዲወገድ በማድረግ ለሌሎችም አርአያ የሆኑትን ግለሰቦች የጽዳት አምባሳደር በማለት የማበረታታት ስራ ተሰርቷል፡፡

### 2.15.4. ቀልዝ (ኮምፖስት) ዝግጅት

በጅማ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ተግባራዊ ሲደረግ ቆሻሻን በየአይነቱ በመለየት ወደሚፈለግበት ቦታ ወስዶ ጥቅም ላይ እንዲውል እየተደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ የሚበሰብስ ቆሻሻን ለብቻ ለይቶ በቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ ባለው ሼድ ውስጥ ቀልዝ(ኮምፖስት) በማዘጋጀት ጥቅም ላይ ማዋል ነው፡፡ ይህ የተዘጋጀ ቀልዝ ለከተማው አረንጓዴ ልማት ስራ በሰፊው በአገልግሎት ላይ እየዋለ ይገኛል፡፡

### 2.15.5. ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘ ሀብት መሆኑ

ቆሻሻ በአግባቡ ከተያዘና ከተጠቀሙበት ሀብት ነው፡፡ የውሃ መያዣ ጠርሙሶችን እና የማዳበሪያ ከረጢቶችን ለችግኝ ማፍያ ፖት በመጠቀም ከቆሻሻነት ወደ ጠቃሚ ማቴሪያል ተለውጦ አገልግሎት መስጠት ችሏል፡፡ ከሚበሰብስ ቆሻሻ ቀልዝ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት በከፍተኛ ዋጋ የሚገዛን የፋብሪካ ማዳበሪያ ተክቶ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡(Effective Micro organizem (E.M)) በማዘጋጀት ለኮምፖስት ዝግጅት ስራ እና ከቆሻሻ የሚመነጩ ሽታዎችን ለመቀነስ እንዲጠቅም ተደርጓል፡፡

### 2.15.6. የኮሪደር ልማት ስራ

በጅማ ከተማ እየተሰራ ያለው የኮሪደር ልማት እስከ 3 ኪ.ሜ ርዝመት እና እስከ 10 ሜ ስፋት ያለው የኮሪደር ልማት ነው፡፡ ለመጠናቀቅም 95% ላይ ደርሷል፡፡ አሁን ባለበት ሁኔታ የኮሪደር ልማቱ በተጠቀሰው ቦታ ላይ በመንገዱ ግራና ቀኝ የአረንጓዴ ልማት ስራ፣ የእግር መንገድ፣የብስክሌት መንገድ፣ ማየት ለተሳናቸው መንገድ፣ በአረንጓዴ አሸብርቀው ሳቢና ማራኪ በሆነ መልኩ የተሰሩ መዝናኛዎች፣ዘመናዊ መብራቶች፣የመኪና ማቆሚያዎች የሚታዩ ሲሆኑ ለቀጣይም የሕዝብ መፀዳጃ ቤቶች፣ካሜራዎች፣ካፍቴሪያሎችና ሌሎችንም ለማሟላት መስመሮቹ የተዘረጉ ናቸው፡፡

ይህ ልማት የከተማዋን ገፅታና ውበት በማሳመር፣ቆሻሻ በአካባቢው እንዳይኖር በማድረግ፣ለሕብረተሰቡ ምቹ እንዲሆን በማስቻል፣በከተማዋ ለጤና ምቹ የሆነ የአየር ንብረት እንዲፈጠር በማድረግ፣በአቧራና በፍሳሽ ቆሻሻ የሚከሰት በሽታ እንዳይኖር በማድረግ ልማቱ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

### 2.15.7. የወንዝ ዳርቻ ልማት ሥራ

በጅማ ከተማ በሁለት ወንዞች ላይ 4 ቦታ የወንዝ ዳርቻ ልማት የለማ ሲሆን ልማቱ በአጠቃላይ 34,063 ካ.ሜ ቦታን ሸፍኗል፡፡ ይህ ቦታ በፊት የቆሻሻ መጣያ ስለነበር ወንዙ እና አካባቢው በቆሻሻ ተበክሎ በሕብረተሰቡ ላይ ከፍተኛ የጤና ጠንቅ ሆኖ ያስቸግር ነበር፡፡ አሁን የወንዝ ዳርቻው ለምቶ ለጤና ምቹ እንዲሁም ሳቢና ማራኪ የሆነ መዝናኛ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል፡፡

# 3. ክፍል ሦስት፡-

## 3.1. ማጠቃለያ

በጅማ ከተማ የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአት ከመጀመሩ በፊት በከተማው የደረቅ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርአቱ በሥርዓት ያልተደራጀ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የከተማው ነዋሪ ከአካባቢው መቆሻሻ የተነሳ በተደጋጋሚ የጤንነት ችግር ይገጥመው ነበር፡፡ በዚህ የተነሳ የከተማ አስተዳደሩ ለችግሩ ትኩረት በመስጠት የመፍትሄ እርምጃ ወስዶ ውጤት አስመዝግቧል፡፡በጅማ ከተማ ከመነሻ አሁን እስካለበት (2017 ዓ.ም) ድረስ የተከናወኑ ሂደቶች እና የተገኙ ውጤቶች ለሌሎችም ትምህርት ይሆናሉ፡፡

የጅማ ከተማ አስተዳደር የተቀናጀ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ የጀመረው  በችግሩ አሳሳቢነት ዙሪያ በአመራርና ባለሙያዎች ደረጃ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ወደ ቀጣዩ ሂደት መራመድ ችለዋል፡፡ የጋራ ዕቅድ በማቀድ፣ ሕብረተሰቡን በማወያየት፣ማህበራትን በማደራጀት፣ግንዛቤ ፈጥሮ ኃላፊነትን በየደረጃው በማከፋፈል አመራሩንና ባለሙያዎችን በማጠናከር ወደ ስራ ገብቷል፡፡በስራው ክንውን ላይ የቅርብ ድጋፍ፣ክትትልና ቁጥጥር በማድረግ የኃላፊነት ሚናውን ተወጥቷል፡፡የተደራጁ ማህበራት ስራቸው በቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ድጋፍ አድርጓል፡፡አካባቢያቸውን በተሻለ ጽዱ ላደረጉ መንደሮች ሞዴል መንደር ብሎ በማበረታታት ለሌላው አርአይ እንዲሆኑ አድርጓል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በዚህ ልክ በመስራቱ ከተማው በፊት ካለበት ችግር እና በቆሻሻ ብክለት ምክንያት ለበሽታ መጋለጥ ስጋት ከመሆን ተላቆ ዛሬ በሌሎችም ሊጎበኙ የሚችሉ ስፍራዎች ያለው ከተማ ሆኗል፡፡ በዕቅድ እየተመራ በቅንጅት በመሰራቱ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፡፡

- በየቦታው ተጥሎ ከተማውን ይበክል የነበረ ደረቅ ቆሻሻ አሁን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል፡፡
- የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (Sanitary Land Fill) ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ተሰርቶ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡
- በፊት በየቦታው ተጥሎ የበሽታ መንስኤ የነበረው ደረቅ ቆሻሻ አሁን ሀብት ሆኖ የገቢ ምንጭ ሆኗል፡፡
- ከደረቅ ቆሻሻ ቀልዝ (ኮምፖስት) በማዘጋጀት ለጥቅም እንዲውል ተደርጓል፡፡
- ሕብረተሰቡ ቆሻሻ ገንዘብ መሆኑን እንዲያውቁት በተግባር አሳይቷል፡፡
- በማህበር የተደራጁ ዜጎች የስራ ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል፡፡
- ቆሻሻን በማጽዳት፣የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችን በመስራት፣የውበትና መናፈሻ ስፍራዎችን በመፍጠር እንዲሁም በየመንደሩ ላሉ ነዋሪዎች ግንዛቤ በመፍጠር አካባቢያቸውን ጽዱና ውብ እንዲያደርጉ ስራ መሰራቱ ለእይታ ከማማሩም አልፎ ከተማው ለጤና ምቹ እንዲሆን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

*“አካባቢያችንን ተንከባከበንና አልምተን ለጤና ምቹ ማድረግ የሁላችንም ኃላፊነት ነው”*